# ክሬዲት-በፈተና ለዓለም ቋንቋዎች ደንቦች

በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የመጀመሪያ ዓመት ከጁላይ 1፣ 2018 በፊት የተመዘገቡ ተማሪዎች፣ የሁለተኛ ዓመት ከጁላይ 1፣ 2019 በፊት፣ ጁኔር(ሦስተኛ ዓመት ) ከጁላይ 1፣ 2020 ዓመት በፊት ወይም ሲኒየር (የአራተኛ ዓመት) ከጁላይ 1፣ 2021 የተመዘገቡ በትምህርት ቦርድ ደንቦች በዝርዝር እንደተገለፀው መደበኛ እና የተረጋገጠ የክሬዲት ነጥብ ማግኘት እንደሚኖርባቸው ይጠይቃል። "አንድ መደበኛ ነጥብ ክሬዲት" ወይም "መደበኛ ክሬዲት" ማለት የተሰጠ ክሬዲት ለወሰደው ኮርስ 140 ሰዓታት ትምህርት ተከታትሎ በሚገባ ላጠናቀቀ እና የኮርሱን መስፈርት ላሟላ ተማሪ የሚሰጥ ነው።

የአሌክሳንደሪያ ከተማ ት/ቤቶች ቦርድ ትምህርት በመከታተል እንደተገኘው ውጤት ካጠናቀቀው ጋር እኩል የሆነ ክሬዲት በተለያየ መንገድ ሊገኝ እንደሚችል ይገነዘባል። በመሆኑም ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ከ6-12 ክፍል ያሉ ተማሪዎች ከእንግሊዘኛ ቋንቋ ሌላ የመነጋገሪያ ቋንቋ ለሚችሉ በዲቪዝን በፀደቀ ብሔራዊ እና አለም አቀፍ መመዘኛ ፈተና እስከ ሶስት (3) መደበኛ (የዓለም ቋንቋ) ክሬዲት ማግኘት ይችላሉ።

## I. በዲቪዝን የፀደቁ መመዘኛዎች

ክሬዲት በፈተና መመዘኛ የተማሪዎችን የውጭ ቋንቋ ብቃት በብሔራዊ ደረጃ በታወቁ እንደ AAPPL፣ OPI እና WPT ለብዙ ቋንቋዎች መለኪያ ያገለግላሉ። **ክሬዲት የሚሰጠው ተማሪዎች ቢያንስ የጀማሪ - ከፈተኛ ብቃት ደረጃ ሲያሳዩ ነው።**

በአስተዳደር ዲቪዝን የፀደቀ መመዘኛ፤

- አንድ ውጥ የሆነ አሰጣጥ አስተዳደር አለው ፣
- በውጭ አካል አግባብነት እንዳለው እና አስተማማኝ እንደሆነ ተረጋግጥል፣
- በሌሎች ስቴቶች እና በአለም አቀፍ አገልግሎት ላይ ውሎል፣
- ከትምህርት ቤት ዲቪዝን ውጪ ነጥብ ይሰጣል፣
- ኮርስ መውሰድ እንዲቀር ጥያቄ(ዌይቨር) ከቀረበበት ኮርስ ዓላማ ጋር የሚጣጣም ስለመሆኑ ተገቢ የጠበቀ ግምገማ ተደርጎበታል።
- በኮምፒውተር ወይም ፈተና በሚወሰድበት ቋንቋ ብቃት ባለው የውጭ ፈታኝ ነጥብ ይሰጣል እና፣
- ተመሳሳይ መደበኛ ክሬዲት(ቶች) ከሚያስገኝ ኮርስ ይዘትና ችሎታ ጋር እኩል የሆነ የዓለም ቋንቋ ብቃትን በትክክል የሚያሳይ

## II. የክሬዲት አሰጣጥ

በተመሳሳይ ኮርስ በተማሪዎች የውጤት ሪከርድ(ትራንስክሪፕት) " አልፎል- P " እንደሚታየው ውጤት ዓይነት በሚገባ የተጠናቀቀ መሆኑን ለማሳየት ተማሪዎች በፈተናው ውጤታማ ከሆኑ "አልፎል- pass" ውጤት ሊያገኙ ይችላሉ ። በተማሪዎች የአጠቃላይ አማካኝ ውጤት (GPA) ላይ ለውጥ የሚያመጣ በፊደል የሚገለፅ ውጤት አያገኙም ።

በዚህ አማራጭ መንገድ የሚገኝ እንደሌላው መደበኛ የክሬዲት ውጤት እኩል በክፍል ደረጃ ፣ በአጠቃላይ አማካኝ ነጥብ፤ በሥርዓተ-ትምህርት በተጨማሪ በሚደረጉ በእጩነት እና በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ትራንስክሪፕት በእኩል ደረጃ ይታያል።

ተማሪዎች በአድቫንስድ ዲፕሎማ መመረቅ ከፈለጉ (ASD) የዓለም ቋንቋ ክሬዲት ማግኘት አለባቸው። እነዚህም ሦስት ዓመት አንድ ቋንቋ በመውሰድ (31) ወይም የሁለት ዓመት /ክሬዲት ሁለት የተለያዩ ቋንቋዎች በመወሰድ (2 x 2) ተማሪዎች መደበኛ ዲፕሎማ የሚወስዱ የአንድ ቋንቋ (2 x 1) በምርጫ የሚወስዱ ኮርሶችን ለማሞላት።

ተማሪዎች ክሬዲት-በፈተና አማራጭ እስከ ሦስት (3) መደበኛ (የዓለም ቋንቋ) ክሬዲት ማግኘት ይችላሉ  በተሰጠው ፈተና በታየው ውጤት መሰረት። ተማሪው በደረጃ III ወይም IV ክፍል ምድብ ባላቸው የቋንቋ ችሎታ ምክንያት ቀደም ሲል ላሉት ደረጃዎች ወደኋላ ክሬዲት ማግኘት ይችላሉ። **ብዙ ክሬዲት ለአንድ ዓይነት የዓለም ቋንቋ ኮርስ መስጠት አይቻልም።**

**ከ6-8 ክፍል ደረጃ ባሉበት ወቅት የዓለም ቋንቋ ክሬዲት ያገኙ ተማሪዎች በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የማይሰጥ በመሆኑ 9ኛ ክፍል እስከሚደርሱ ድረስ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ምድብ አይመደቡም ።**

ፈተናው በኮምፒውተር ወይም ከት/ቤት ውጭ በመፈተኛ ቋንቋው ብቃት ባለው ገምጋሚ ሰው ይታረማል። ውጤቱም የመጨረሻ ይሆናል እና ይግባኝ አይኖረውም። ክሬዲት የሚሰጠው በሚከተለው ሁኔታ ነው።

| **የብቃት ደረጃ** | **የሚሰጠው ክሬዲት ነጥብ** | **ቀጠይ ኮርስ ምድብ** | **የኤስ.ኤች.ኤስ (SHS)* ቀጣይ ምድብ** |
|---|---|---|---|
| ጀማሪ-ከፍተኛ | 1.0 | ደረጃ III | ኤስ.ኤች.ኤስ - II |
| መካከለኛ- ዝቅተኛ | 2.0 | ደረጃ IV | ኤስ.ኤች.ኤስ - III |
| መካከለኛ- ዝቅተኛ | 3.0 | ከፍተኛ ርእሶች(AP) | ከፍተኛ ርእሶች(AP) |
| መካከለኛ- ከፍተኛ | 3.0 | ኤ.ፒ. (AP) ወይም ከፍተኛ ርእሶች (ለቻይንኛ፣ፈረንሳይኛ እና ጀርመንኛ ቋንቋዎች የሚሰጥ)፣ የሚመለከተው ከሆነ | ኤ.ፒ. (AP) የሚመለከተው ከሆነ |
| ከፍተኛ- ዝቅተኛ | 3.0 | አይመለከተውም | አይመለከተውም |
| ከፍተኛ- መካከለኛ | 3.0 | አይመለከተውም | አይመለከተውም |
| ከፍተኛ- ከፍተኛ | 3.0 | አይመለከተውም | አይመለከተውም |
| ምርጥ | 3.0 | አይመለከተውም | አይመለከተውም |
| ልዩ ችሎታ | 3.0 | አይመለከተውም | አይመለከተውም |

*በቤት ቋንቋቸው ስፖኒሽ ተናጋሪዎች (ኤስ.ኤች.ኤስ - SHS)

የመመዘኛ ዘዴው አንድ ዓይነት በላይ አቀራረብ ካለው ( ማለትም፤ መስማት፣ ማንበብ፣ መናገር፣ እና መፃፍ ) እና ለእያንዳንዱ የመመዘኛ የራሱ ነጥብ የሚሰጥ ከሆነ ክሬዲት ለመወሰን የሚወሰደው  ነጥብ ዝቅተኛው ነው። (ለምሳሌ፣ አንድ ተማሪ የሚከተሉትን ነጥቦች አግኝቶል፤  መስማት-  መካከለኛ 2 ፣ ንባብ-  መካከለኛ 3፣ ፅሁፍ- መካከለኛ 1፣ መናገር- መካከለኛ 3፣  ከዚያም  የሚሰጠውን ክሬዲት ለመወሰን መካከለኛ 1 የተገኘው ፅሁፍ ውጤት ይወሰዳል ።)

## III. እጩነት

ከክፍል 6-12 ያሉ ተማሪዎች  ፈተና በሚወስዱት ቋንቋ  ማንበብ፣ መናገር እና መስማት ከቻሉ ፈተና በመውሰድ ክሬዲት የማግኘት እድል አላቸው። ተማሪዎች ሁሉም የሚሰጣቸውን ስራ ራስቸውን ችለው ስራውን ጀማሪ-ከፍተኛ ወይም ከዚያ በላይ ባለ ደረጃ ማከናወን አለባቸው። ለምሳሌ ተማሪዎች ፈተና በሚወስዱበት ቋንቋ የሚከተለውን ማድረግ መቻል አለባቸው፤

- ቀላል ጥያቄዎች መጠየቅ እና መመለስ፣
- ከሌላ ሰው ጋር ሲነጋገር በቀላል ዓርፍተ ነገሮችን መግለፅ፣
- ቀላል መሰረታዊ መረጃዎችን መለዋወጥ፣
- የሚወዱትን እና የሚጠሉትን መግለፅ፣
- ቀላል መሰረታዊ ቅፃችን መሙላት፣ እና፣
- ቀላል መሰረታዊ የእለታዊ እንቅስቃሴዎችን ማንበብ እና መፃፍ።

ክሬዲት-በፈተና ማግኘት የሚፈልጉ ተማሪዎች በኤሌክስንደሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የሥርዓተ ትምህርት እና የትምህርት አሰጣጥ መምሪያ ድረ ገፅ ላይ ያለውን የራስ መመዘኛ ግሪድ በቅድሚያ ማጠናቀቅ አለባቸው ።

**ከታች የተገለፀውን በክፍል V መመዘኛ ምትክ በዓለም ቋንቋ የተመዘገቡ ተማሪዎች ደረጃ IV ወይም በስፖኒሽ በቤታቸው ለሚናገሩ III ኮርስ የAAPPL ፈተና መውሰድ ይችላሉ በትምህርት ዓመቱ መጨረሻ። ያን ፈተና መወሰድ የጥምር ቋንቋ ተናጋሪ (Seal of Biliteracy) የዓለም ቋንቋ መስፈርት ለማሟላት ያስችላል።**

የጀማሪ - ከፍተኛ ብቃት ደረጃ ወይም ከዚያ በላይ ያገኙ ተማሪዎች የዓለም ቋንቋ ክሬዲት (ለዝቅተኛ -ደረጃ የቋንቋ ኮርስ) ሊያገኙ ይችላሉ በመጀመሪያ በከፍተኛ ደረጃ የቋንቋ ኮርስ የተመደቡ ከሆነና ለከፍተኛ (አድቫንስድ) ዲፕሎማ ተፈላጊውን ክሬዲት ካላሟሉ።

**ክሬዲት-በፈተና ውጤት ቀደም ሲል በፈተና የወደቁትን ኮርስ ወደማለፊያ ነጥብ መቀየር አይችልም።**

## IV. የፈተና አሰጣጥ

ተማሪዎች በኦንላይን በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የካሪከለም እና የትምህርት አሰጣጥ ዲፖርትሜንት ድረገፅ መመዝገብ ይችላሉ። ከዚያም የፈተናው ቀን፣ ሰዓት እና ቦታ ለማረጋገጥ ከተማሪዎች ጋር ግንኙነት ይደረጋል።

እድሚያቸው ከ18 ዓመት በታች ለሆኑ ተማሪዎች ወላጅ(ች)፣አሳዳጊ(ዎች)፣ ወይም የተማሪ ትምህርት አማካሪ የኤሌክትሮኒክስ ፊርማ መፈረም ይኖርባቸዋል በማመልከቻው ላይ የቀረበው መረጃ ትክክለኛ መሆኑን ለማረጋገጥ።

ተማሪ ክሬዲት-በፈተና ውጤት ለማግኘት መሞከር የሚችሉት በአመት አንድ ጊዜ ብቻ ይሆናል። አንድ ዋና ፈተና ቀን በፎል እና አንድ የማካካሻ ቀን በስፐሪንግ ወቅት ይኖራል። (ለስፐሪንግ ወቅት ምዝገባ የዓለም ቋንቋ ትምህርት ባለሞያ ማፅደቅ ይኖርበታል። ወደ ትምህርት ቤት ክልሉ የተዛወሩ ሲኒየር (አስራ ሁለተኛ ተማሪዎች) በአመቱ አጋማሽ ፈተና በስፐሪንግ ወቅት መውሰድ ይችላሉ። ሁለቱም የሚሰጡት የተማሪዎች ቀን ባልሆኑ (ማለትም አስተማሪዎች የስራ ቀናት ) ይሆናል። **የመመዘኛ ፈተና ግምገማ ለኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ተማሪዎች ያለምንም ክፍያ ለመጀመሪያ ጊዜ ለአንድ ቋንቋ ይሰጣል። የድጋሚ ፈተና በተማሪው ወጪ ይሆናል ዋጋውም እንደ ፈተናው ይለያያል።**

ወላጆች/አሳዳጊዎች የተማሪዎቻቸው ውጤት በፖስታ ቤት በኩል ይደርሳቸዋል።

## V. ለፈተና አሰጣጥ ምቹ ሁኔታዎች

የአካል ጉዳት ያላቸው ሁሉም ተማሪዎች እና ለእንግሊዘኛ ቋንቋ (EL) የተመረጡ ተማሪዎች በስቴት እና በፌደራል ህግ መመሪያ መሰረት የፈተና አሰጣጥ በተገቢው አመቺ ሁኔታ ይዘጋጃል።

<u>የአካል ጉዳት ያላቸው ተማሪዎች</u>

የአካል ጉዳት ባላቸው ተማሪዎች ክሬዲት-በፈተና አወሳሰድ በተማሪው የግል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ወይም 504 እቅድ መሰረት ይከናወናል።

<u>የእንግሊዘኛ ቋንቋ ተማሪዎች</u>

ለእንግሊዘኛ ቋንቋ ተማሪዎች(EL) የቤት መነጋገሪያ ቋንቋቸው አረብኛ እና ስፖኒሽኛ እና በደረጃ 1 ወይም በደረጃ 2 በ WIDA Access for ELLs ፈተና ካገኙ የድጋፍ አሰጣጥ ይደረጋል የፈተናው መግለጫ በተማሪው የቤት ቋንቋው እንዲሆን። ለብዙዋቹ ፈተናዎች መግለጫው እና መመሪያዋቹ በእንግሊዘኛ ናቸው።

## VI. የዓለም ቋንቋ ምዘና መስጠት

ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. በአሁኑ ወቅት ክሬዲት-በፈተና ለሚከተሉት ይሰጣል፤

| **ቋንቋዎች** | **የመመዘኛው ብቃት** | **የወቅቱ ዋጋ ለድጋሚ ፈተና** |
|---|---|---|
| አረበኛ፣ ቻይንኛ ፣ ፈረንሣይኛ፣ ጀርመንኛ፣ ህንዲ፣ ጣሊያንኛ፣ ጃፖንኛ ኮሪያ፣ ፖርቹጊኛ፣ ሩሲያኛ፣ ስፖኒሽኛ፣ ታይ | ACTFL የችሎታ ብቃት መመዘኛ ለውጭ ቋንቋዎች ብቃት(AAPPL) (የትርጎሜ መስማት እና ማንበብ ፣ የእርስበርስ መደማመጥ እና መነጋገር/ የሃሳብ መግለጫ ፅሑፍ) (በኮምፒውተር ላይ የተመሰረተ) | $15። |
| አልባኒያ (መፅሐፍ ብቻ ) ፣ ካንቶኒስ ቻይንኛ፣ ዳኒሽ ፣ ግሪክ (ዘመናዊ) ሃይቲ ክሬዋል(መፅሐፍ ብቻ)፣ ኢብራይስጥ(ህብሪው)፣ ኖርዌይ፣ ፐርዚያ ፋርስ ፣ ፖላንድ፣ ቱርክ፣ ቬትናም። | የፅሑፍ ብቃት ፈተና (በኮምፒውተር ላይ የተመሰረተ) | $70። |
| ቤንጋሊ፣ ኢንዶኔዝያ፣ ፖሽቶ፣ የብራዚል ፖርቹጋል | የንግግር ብቃት ቃለመጠየቅ (በኮምፒውተር ላይ የተመሰረተ) | $105። |
| አፍሪካን፣ አካንቲዊ፣ አርመን፣ አሲሪያን፣ አዘርባጃን፣ ባሉቺ፣ ቦስኒያን፣ ቡልጋሪያን፣ በርማ፣ ካምቦዲያን፣ ሲቦናኖ፣ ቻቫካኖ፣ ቼክ፣ ዳሪ፣ ደች፣ ፊኒሽ፣ ጋአ፣ ጆርጂያን፣ ጉጅራቲ፣ ሐውሳ፣ ህብሪው፣ ሐሞንግ-ሞንግ፣ ሐንጋሪያን፣ ኢአካኖ፣ ኢንዶኔዝያ፣ ኢራቅ፣ ጃቫኒስ፣ ካዛክ፣ ኪኮንጎ-ኮንጉ፣ ኪኒያዋንዳዕ ፣ ኪሩንዲ፣ ኮሪያን ፣ኪሮ፣ ኩርዲሽ-ክራማንጂ፣ ላኦ፣ ሌቫንቲን፣ ሊንጋላ፣ ማሌ፣ ማሌአላማ፣ ማንዲንጎ-ባምባራ፣ ሞንጎሊያ፣ ኔፖሊ፣ ኖርዌጂያን፣ ፑንጃቢ፣ ሮማኒያን፣ ራሺያን ፣ ስርቦ_ክሮሺያን፣ ስንድሂ፣ ሲንሃሊስ፣ ስሎቫክ፣ ሶማሊኛ፣ | የንግግር ብቃት ቃለመጠየቅ | $119 - $139 |

| | | |
|---|---|---|
| ስፓኒሽኛ፣ስዋሂሊኛ፣ ስዊዲን፣ ታጋሎግ፣ ታጂክ፣ ታሚል፣ ታስግ፣ ተሉጉ፣ ታይ፣ ቱርክሜን፣ ኡግር፣ ዩክሬኒያን፣ ኡርዱ፣ ኡዝቤክ፣ ዋልፍ፣ ዮርባ፣ ዝሉ፡ | | |
| የአሜሪካ የምልከት ቋንቋ (ASL) | የአሜሪካ የምልከት ቋንቋ ብቃት ቃለመጠየቅ | በአካል በመገኘት $165 - በቪዲዮፎን ከፈታኝ ጋር $185። |

ወደፊት ሌሎች ቋንቋዋች በብሔራዊ ደረጃ መመዘኛ ከተዘጋጀላቸው ከላይ የተገለፀው ሊቀየር ይችላል። በተጨማሪም ከሌሎች የትምህርት አስተዳደሮች ጋር የመተባበር እድሉ ከተፈጠረ ክሬዲት በፈተና ለተጨማሪ ቋንቋዋች በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የማይሰጡ በሌሎች የትምህርት አስተዳደሮች በሚሰጡ መመዘኛዋች ሊሰጡ ይችላሉ። በእንደዚህ ሁኔታዋች የሚሰጠው የክሬዲት ብዛት የትምህርት አስተዳደሩ ፖሊሲ በሚፈቅደው መሰረት ሊስተካከል ይችላል።

## VII. የጥምር ቋንቋ ተናጋሪ ማህተም (Seal of Biliteracy)

የትምህርት ቦርዱ ከ2015-16 ጀምሮ የሚሰጠው የጥምር ቋንቋ ተናጋሪ ማህተም የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተመራቂ ከእንግሊዘኛ በተጨማሪ በአንድ ወይም ከዚያ በላይ ቋንቋዋች ከፍተኛ ብቃት እንዳለው/እንዳላት የምስክርነት ማረጋገጫ ይሰጣል። የጥምር ቋንቋ ተናጋሪ ማህተም (Seal of Biliteracy) የሚሰጠው ሁሉም ፈተናዋች ላለፉ ተማሪዋች በኮርስ መጨረሻ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ብቃት ባለው ወይም ከዚያ ከፍ ባለ ደረጃ (11ኛ ክፍል የቨርጂኒያ የደረጃ መመዘኛ (SOL) እና በአንድ ሌላ ቋንቋ በመካከለኛ - መካከለኛ ደረጃ ወይም ከዚያ በላይ በብሔራዊ ደረጃ በሚዘጋጅ ፈተና ውጤት ከገኙ የጥምር ቋንቋ ተናጋሪ ማህተም የሚሰጠው በሁለተኛ ደረጃ ዲፕሎማ በሚደረግ ማህተም ነው።

## VIII. ይግባኝ

ክሬዲት-በፈተና ምዘና የመጨረሻ ሲሆን የይግባኝ ጥያቄ ማቅረብ አይቻልም።

የፀደቀው፤ ኤፕሪል 26 ቀን 2018
የተሻሻለው፤ ሜይ 1፣ 2018
የተሻሻለው፤ ሴፕቴምበር 7፣ 2018

የሕግ ማጣቅሻ፤ የቨርጂኒያ ህግ 1950 እንደተሻሻለው § 22.1-253.13:4.

(8) -131-110

ለምረቃ መስፈርቶች መመሪያዋች ፣ የየአካባቢው አማራጭ መንገድ መደበኛ የክሬዲት ውጤት፣ የቨርጂኒያ የትምህርት ቦርድ(ኦክቶበር 2015)

የቃላት መፍቻ፤ IAA የትምህርት ዓለማ ማሳወቂያ
IGBG በቤት ውስጥ መረጃ መለዋወጫ እና አማራጭ የትምህርት አሰጣጥ
IGBGA በኦንላይን የሚሰጥ የትምህርት ዘዴ እና ቨርችዋል የትምህርት ፕሮግራም
IGBF የእንግሊዘኛ ቋንቋ ተማሪ (EL)
IKEB ክፍል መዝለል

IKF የቨርጅኒያ መመዘኛ ፕሮግራም እና የመመረቂያ መስፈርቶች
IKF-R የቨርጅኒያ መመዘኛ ፕሮግራም እና የመመረቂያ መስፈርቶች ደንቦች
IKFD አማራጭ መንገድ መደበኛ የክሬዲት ነጥብ ለማግኘት
ክሬዲት-በፈተና ለዓለም ቋንቋዎች ደንቦች
JO የተማሪ ሪከርድ ማህደር